# የሮሜ መጽሐፍ (18ሀ)

## ጥናት አንድ (ሮሜ 1:1-17)

የጥናት ዓላማ:- ወንጌል ሰዎችን ሁሉ ለማዳን የሚችል የእግዚአብሄር ሃይል ያለበት መልዕክት ስለሆነ ልናፍርበት እንደማይገባን ለማበረታታት::
የምናሰላስለው ጥቅስ: «በወንጌል አላፍርም ምክንያቱም ለሚያምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሄር ሃይል ነው::» ሮሜ 1:16

1. ሮሜ 1:1-17 በአንድነት ይነበብ:: በዚህ ክፍል በቁጥር በብዛት በመደጋገም የተጠቀሰ አንድ ቃል ምን እንደሆነ ተናገር:: የዚህ ቃል መደጋገም ምን ያናገረናል?
2. ከቁ1-6 ትን በመመርኮዝ ወንጌል ለሚለው ሃሳብ በአጭሩ ትርጉም ስጥ ብትባል ምን ትላለህ?
3. ወንጌልን በተመለከተ ቁጥር 2 ምን ይናገራል? ይህ ቁጥር ስለ ወንጌል የሚመልሰው ጥያቄ ምንድነው? ይህስ ጥያቄ ሊጠየቅ የሚችለው በማን ይመስልሃል?
4. በቁ 6 እና 7 መሰረት ስለ ሮሜ ሰዎች የምትገነዘባቸውን እውነቶች ዘርዝር::
5. ቁ 8 «እምነታችሁ በዓለም ሁሉ በመሰማቱ...» በዘመናችን ስለ ቤተክርስትያን ከርቀትም ሆነ ከቅርብ ከምትሰማቸው ነገሮች ጋራ ይህንን በማነፃፀር ተናገር::
6. ቁ 3 «ወንጌሉም ስለ ልጁ» ቁ9 «የልጁን ወንጌል» ከሚሉት አባባሎች ምን የምትረዳው እውነት አለ?
7. ሐዋርያው ወደ ሮም ለመሄድ ፍላጎት እንዳለው እናነባለን:: በቁ 10-13 መሰረት ወደዚያ መሄድ የመፈለጉ ምክንያቶች ምን ምንድናቸው? ከነዚህ ውስጥ በአንተ አመለከከት ጎልቶ የሚታይ ከለ ለወገኖች አከፍል::
8. ቁ 10 «በእግዚአብሄር ፈቃድ ወደ እናንተ እንድመጣ ... እጸልያለሁ» ከዚህ ጥቅስ በፀሎት ውስጥ የእግዚአብሄር ፈቃድ ሊኖረው ስለሚገባው ቦታ ምን ትማራለህ?
9. በ1:13 ላይ የሚናገረው መከልከልና በ1ኛ ተሰ 2:18 በመናነበው መሃል ልዩነት ያለ ይመስልሃል ወይ? መልስህን አብራራ::
10. ቁጥር 16 እና 17 በወንጌል የማያፍር ሰው የተረዳቸው ሶስት ነገሮች ነገሮችን ይጠቁመናል:: እነዚህ ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
11. አንተስ በወንጌል አላፍርም ብለህ በድፍረት መናገር ትችላለህ ወይ? በምን ዓይነት ወገኖች በፀሎት እንዲረዱን እንደምንፈልግ በመነጋገር እርስ በእርሳችሁ ተፀላለዩ::

# ጥናት ሁለት (ሮሜ 1:18-32)

የጥናት ዓላማ:- እግዚአብሄር እራሱን የሚገልጽልን ምክንያት የተሻለና መረዳት ያቀበት አምልኮ እንድናቀርብለት እንደሆነ ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «እግዚአብሄርን ቢያውቁም እንክ እንደ አምላክነቱ አላከበሩትም፤ ምስጋናም አላቀረቡለትም::» ሮሜ 1:21

1. ሮሜ 1:18-32 በአንድነት ይነበብ:: በቁ 18-20 ስለ እግዚአብሄር ባህርይ የምታያቸውን ቢያንስ ሶስት ነገሮች ዘርዝር::
2. «እውነትን ዐፍነው በሚይዙ...» የሚለው አባባል ስለ ምን አይነት እውነት ነው የሚናገረው? በእኛ ህይወትስ እውነት ሊታፈን የሚችልበት ሁኔታ ታያለህ ወይ? አስረዳ::
3. በዚህ ምንባብ ውስጥ እግዚአብሔርን አለማክበርራቸውና አለማመስገናቸው ያስከተላቸውን ነገሮች ዘርዝር:: እነዚህን ሰዎች ሞኝ ያሰኛቸው ነገርስ ምንድነው ትላለህ?
4. እግዚአብሄርን በማወቅና በአምልኮ (ማክበርና ማመስገን) መሃል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ምን ታያለህ? ቁ 21
5. ቁ 24 ቁ 26 እና ቁ28 ትን በማንበብ እነዚህን ሰዎችን ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ እንዲሰጥ እግዚአብሄርን ያስገደደው ነገር አለ ትላለህ ወይ? ምላሽህን አስረዳ:: አሳልፎ መስጠት የሚለውንስ ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ:
6. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግብረ ሰዶም አይናገርም ወይም ደግሞ ቢናገርም ግልጽ አይደለም ለሚለው አባባል ከዚህ ምንባብ ውስጥ ምን ምላሽ የሚሆን ነገር ተመልክተሃል?
7. ቁ 21 ንና ቁ 28 ትን በማንበብ እግዚአብሄርን ማወቅን በተመለከተ ስላላቸው ሁለት አይነት አመለከከት እና የእግዚአብሄርን እውነት ያፈኑበትንም ሁኔታ በመጨመር ተነጋገሩበት::
8. በቁጥር 32 ላይ የምናነበው ሃጥያት በምንባቡ ከተዘረዘሩት ሃጥያቶች ሁሉ የሚለየው በምን መንገድ ነው?
9. የእግዚአብሄርን እውነት በይበልጥ ባወቅህ ቁጥር ወደ አምልኮ ሲመራህ ታገኘዋለህ ወይ? እግዚአብሄር እውነትን ገልጦልን በዚያ እውነት አለመጠቀም ስለሚያሳዝነው እርሱን ማወቅህ ለአምልኮ እንዲሆንልህ ጸልይ::

# ጥናት ሶስት (ሮሜ 2:1-29)

የጥናት ዓላማ:- ከቃሉ ተቃራኒ የሆነ ህይወት ስንኖር በአህዛብ ፊት ለእግዚአብሄር ስም መሰደቢያ እየሆንን እንደሆነ እንዳንዘነጋ ለማሳሰብ::
የምናሰላስለው ጥቅስ: «በእናንተ ምክንያት የእግዚአብሄር ስም በአህዛብ ዘንድ ይሰደባል::» ሮሜ 2:24

1. «...የምታመከኝበት የለህም» ቁ1 የተባለው ሰው ለምንድነው የሚያመከኘው የማይኖረው?
2. ቁ1-5 ስለ እግዚአብሄር ፍርድ የሚስረዳን አንድ እውነት ምንድነው? ይህ ዓይነቱ የፍርድ አይነት ከሰው ፍርድ በምን መንገድ ይለያል ትላለህ?
3. አንድ አይሁዳዊ ምዕራፍ አንድን ብቻ ቢያነብ የሚሰማው ስሜት ምን ይመስላል? ምዕራፍ ሁለትን ሲያነብስ ስሜቱ የሚቀየር ይመስልሃል ወይ? ለምን?
4. በቁ4 መሰረት እግዚአብሄር ያሳያቸውን ቸርነትና ትዕግስት የእስራኤል ልጆች እንዴት ነው ነበረ የተረዱት? በእኛ ህይወት ቸርነቱንና ትዕግሥቱን ለድርጊታችን ተቀባይነት ማረጋገጫ አድርገን የምንወስድባቸው ጊዜያት አሉ ወይ? ተነጋገሩባቸው::
5. ቁ9-11 ስለ እግዚአብሄር ባህርይ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው? ሐዋርያው ይህንን ባህርይ በዚህ ሥፍራ ማጉላት የፈለገው ለምን ይመስልሃል?
6. ህግ ባላቸው አይሁድና ህግ በሌላቸው በአህዛብ መሃል ስለሚኖረው የፍርድ ሁኔታ ቁ12-14 የሚነግረን ዋነኛ ሃሳቦች ምን ምንድናቸው?
7. በቁ15-17 መሰረት ክርስቶስ በሚፈርድበት ጊዜ ህግ ስላልነበራቸው ሰዎች ግልጽ የሚሆኑ ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር::
8. ቁ17-20 ሲጀምር አይሁዳዊነታቸውን እያወቀ «አንተ ይሁዲ ነኝ ከልክ...» በማለት የጀመረበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? ይህንኑ ክፍል ስታነብ አይሁዶች ስለራሳቸው ማንነት ምን ይላሉ?
9. ቁ21-23ትን በአንድ ቃል ከልሆነ ደግሞ በአጭር አረፍተ ነገር ግለጽ:: ለምንድነው ይህ የተናገርከው ሃሳብ ለእግዚአብሄር ስም መሰደቢያ ሊሆን የሚችለው?
10. በቁ 25-29 በምናነበው መግለጫ መሰረት ግርዛት ምንድነው? አይሁዳዊነት የተስፋው ቃል ባለቤትነትን ግርዛት ደግሞ የባለቤትነት ምልክት ከሆነ እኛ ከዚህ ተስፋ ተከፋይ ነን ወይ? ከሆንስ አረማመዳችን ለእግዚአብሄር ስም መሰደቢያ ወይስ ማስከበሪያ?

# ጥናት አራት (ሮሜ 3፡1-20)

የጥናት ዓላማ፡- አህዛብ ሆነ አይሁዳዊ ወይም የሞራል ሰው ማናችንም ከማናችንም የተሻልን እንዳልሆንና የእግዚአብሄር ቸርነትና ምህረት ብቻ ለደህንነት ሊያበቃን እንደሚችል ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እንግዲህ ምን እንላለን? እኛ ከእነርሱ እንበልጣለንን? ከቶ አይደለም፤ አይሁድም ሆኑ አህዛብ ሁሉም ከሃጥያት በታች እንደሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋል፡፡›› ሮሜ 3፡9

1. ሮሜ 3፡1-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ 3፡1-8 ሃዋርያው እየተነጋገረ ያለው ከማን ጋራ ነው? የአይሁዳዊ ጥቅም ብሎ እርሱ የጠቀሰው ነገር ምንድነው? ከዚህ በተጨማሪ ሮሜ 9፡4-5 ትን አንብብና በተጨማሪነት ሊጠቀሱ የሚችሉትን ነገሮች ተናገር፡፡
2. በቁጥር 9 መሰረት ሃዋርያው ማጠቃለያ አድርጎ ያሰፈረው ሃሳብ ምንድነው? ቁ1 አይሁዳዊነት ጥቅም አለው ሲል ቁ9 ደግሞ አይሁዳዊ ብልጫ የለውም ይላል እነዚህ ሃሳቦች ቅራኔ አላቸው ወይ? አስረዳ፡፡
3. «እኛ ከእነርሱ እንበልጣለንን?» በማለት ሲናገር «እኛ» ሲል እነማንን ነው? «እነርሱ» ሲልስ?
4. «ሁሉም ከሃጥያት በታች እንደሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋል፡፡» ከሃጥያት በታች መሆን ማለት ምን ማለት ነው?
5. በምዕራፍ አንድ ውስጥ እነዚያን ሁሉ የሃጥያት አይነቶች ዘርዝሮ እዚህ በቁ 9 ላይ ከሃጥያት በታች በማለት በነጠላ አጠራር የሚጠራው ለምንድነው?
6. በ3፡10-18 ውስጥ በመጀመሪያ እነዚህ ሰዎችጋ የሉም የሚላቸውን ስድስት ነገሮች በየተራ ዘርዝር፤ ከዚያም አሉ የሚላቸውን ስድስት ነገሮች ደግሞ ዘርዝር፡፡
7. ዛሬ ያጠናነው ክፍል ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሄር ፊት ሲታዩ ስላላቸው አቋም ምን ይነግረናል? ከዚህ በመነሳት የተገለጠው የእግዚአብሔር ማዳንስ የሚያስፈልገው ለማነው ማለት እንችላለን?
8. ራስህን ከሌላው እንደተሻልክ ተሰምቶህ ያውቃል ወይ? የዛሪው ትምህርት አመለካከትህን የቀየረበት መንገድ ካለ ለወገኖች አካፍል፡፡

# ጥናት አምስት (ሮሜ 3:21-31)

የጥናት ዓላማ:- እግዚአብሄር ሃጥያተኞችን ሲያጸድቅ የራሱን ጻድቅ ፈራጅነት እንደጠበቀ ሆኖ መሆኑን ግልጽ ለማድረግ::
የምናሰላስለው ጥቅስ: «...እርሱ ራሱ ጻድቅ ሆኖ በኢየሱስ የሚያምነውን የሚያጸድቅ መሆኑን ለማሳየት ነው::» ሮሜ 3:26

1. ሮሜ 3:21-31 በአንድነት ይነበብ:: በዚህ ምንባብ ውስጥ ለክፉና ለመልከም ዜና መገናኛ ድልድይ አድርገህ የምታያቸው ሁለት ቃላት ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር::
2. ቁ21 «ከህግ ውጭ የሆነ» ሲል ምን ማለቱ ነው? ስለዚህ ጽድቅስ ህግና ነብያት መመስከራቸው ለአንባቢያኑ ምን ያረጋግጣል?
3. ከቁ21-22 ያለው ክፍል የእግዚአብሄርን ጽድቅ በተመለከተ የሚመልሳቸውን ቢያንስ ስድስት ነገሮች ዘርዝር::
4. ለምንድነው ቁ 22-23 ልዩነት የለም ያለበት ምክንያት? ሃጥያትንና የእግዚአብሄር ክብር መጉደልን ያገናኘበት ምክንያት ለምንድነው?
5. ቁ 25-26 ኢየሱስን መስዋዕት አድርጎ ያቀረበው የራሱን ጽድቁን ለማሳየት ነው ይላል:: በክርስቶስ መስዋዕትነት የእግዚአብሄር ጽድቅ ሊታይ የሚችለው እንዴት ነው?
6. ለመዳን መንገዱ አንድ ነው የሚለውን ሃሳብ ከቁጥር 27-31 ያለው ክፍል እንዴት ያጠናክራል?
7. ደህንነት በእምነት ብቻ ከሆነ ህግ ዋጋ አያጣም ወይ? «ህጉን እናጸናለን» የሚለውንስ አባባለ እንዴት ትረዳዋለህ?(31)
8. አንተንና እኔን ጻድቅ ለማድረግ በልጁ ላይ መጨከን እንደነበረበት ምን ያህል ትረዳለህ? ይህንን ክፍል በማጥናትህ የተረዳኸው አዲስ እውነት ካለ ለወገኖችህ አካፍል:: ጽድቅን በነጻ አገኘን እንጂ ለእግዚአብሄር ውድ ዋጋ እንዳስከፈለው አንርሳ::

# ጥናት ስድስት (ሮሜ 4:1-25)

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄርን ስናምነው በጭፍን ሳይሆን ከፊታችን የተጋረጠውን እንቅፋት ሁሉ ምን እንደሆነ አውቀንና ተረድተን ነገር ግን እግዚአብሄር የገባው የተስፋ ቃል ከዚያ ሁሉ ይበልጣል ማለታችን እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ: «..የራሱም ሰውነት ሆነ የሳራ ማህፀን ምውት እንደነበረ እያወቀ በእምነቱ አልደከመም፡፡» ሮሜ 4:19

1. ሮሜ 4:1-25 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ 1-3 ላይ አብርሃም የሚፎክርበት ነገር እንዳለውና እንደሌለው በማረጋገጫነት ለመጠቀም ያቀረበው ነገር ምንድነው? ከዚህ ለህይወታችን ልንማር የምንችለው ነገር ምን እንደሆነ ተወያዩበት፡፡
2. ቁ 4-5 ባለው ክፍል ውስጥ ሥራ እያለ የሚናገረው ምን አይነቱን ሥራ ነው? በ1ኛ ተሰ ላይ የማይሰራ አይብላ ከሚለው ጥቅስ ጋራ እንዴት ታገናዝበዋለህ? እግዚአብሄር አለመስራትን ያደፋፍራል ወይ?
3. በዚህ ምንባብ ውስጥ ሁለቱን ማለትም አብርሃምንና ዳዊትን ያመጣበት ዋነኛ ምክንያት ምንድነው ትላለህ? ከዳዊት ነፍሰ ገዳይነት፤ ዝሙትና ውሸት ጋራ ይህ ሃዋርያው የሚናገረው አስተሳሰብ እንዴት ሊሄድ እንደሚችል አስረዳ፡፡
4. በቁ 9-12 አብርሃም የጸደቀበትን ጊዜ ማለትም ከመገረዙ በፊት ወይም በኋላ መሆኑን ለአድማጮቹ ማረጋገጥ ለምን አስፈለገው?
5. «ምንም ተስፋ በሌለበት አብርሃም በተስፋ አምኖ የብዙ ህዝብ አባት ሆነ፡፡»ቁ18 ይህ ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩበት፡፡ አብርሃም በተስፋ ያመነው ምኑን ነው? ከዚህ ለእኛስ ልንወስድ የምንችለው ትምህርት ምንድነው?
6. «እያወቀ በእምነት አልደከመም» የሚለው አነጋገር የአብርሃምን እምነት ይበልጥ አስደናቂ የሚያደርገው ለምንድነው?
7. በቁጥር 25 መሰረት በኢየሱስ ሞት እኛ ያገኘነው ነገር ምንድነው? በትንሳኤውስ ምን ተገኘ ይለናል? በነዚህ ሃሳቦች ላይ ሰፋ አድርጋችሁ ተነጋገሩባቸው፡፡
8. ቢያማችሁም አመመኝ አትበሉ፤ ብትቸገሩ መቸገራችሁን አትናገሩ በማለት ይህንን አይነቱን ሃሳብ ማስተናገድ የእምነት ማነስ እንደሆነ የምንሰማው ትምህርት ከአብርሃም ህይወት ጋር እንዴት ታየዋለህ? እኛም ያለንበትን ከባድ ሁኔታ ሁሉ አውቀንና ተረድተን በእግዚአብሄር ተስፋ ቃል መቆም መለማመድ ይኖርብናል፡፡

# ጥናት ሰባት (ሮሜ 5:1-11)

የጥናት ዓላማ፦ መከራ ሲገጥመን እግዚአብሄር እንደተቆጣብን አድርጎ ማቁጠር የሰሳሳተ አስተያየት መሆኑንና ይልቁን የልጁን መልክ እንድንመስል እኛን ለመስራት የሚጠቀምበት መሳሪያ እንደሆነ ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «የእግዚአብሄር ጠላቶች ሳለን በልጁ ሞት ከእርሱ ጋራ ከታረቅን፤ እርቅን ከገኘን በኋላ በህይወቱማ መዳናችን እንዴት የላቀ አይሆንም!» ሮሜ 5:10

1. ሮሜ 5:1-11 በአንድነት ይነበብ:: በቁ 1-5 ባለው ክፍል ውስጥ በእምነት የመጽደቃችን ውጤቶች ሆነው የተጠቀሱ ቢያንስ ሶስት ነገሮችን ዘርዝር::
2. በሮሜ 5:1-11 ውስጥ «ሐሴት እናደርጋለን» ብሎ የሚናገርባቸው ሶስት ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር::
3. በተራ ቁጥር 2 ላይ ከተጠቀሱት ሶስት ሃሳቦች መሃል በሰዎች አስተሳሰብ ሃሴት ሊደረግበት የማይገባው የትኛው ነው? አማኝ በመከራ እንዴትና ለምንድነው ሐሴት ማድረግ የሚችለው?
4. መከራ ብቻውን የተፈተነ ባህርይን ያስገኛል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ለማለት እንደቻልክ አስረዳ::
5. ያመነም ያላመነም በመከራ ውስጥ እንደሚያልፍ ይታወቃል:: ማንኛውም ሰው መከራ ሲገጥመው ሊቀበል የሚችልባቸውን የተለያዩ መንገዶች ተወያዩባቸው:: የአማኝ መከራን አቀባበል ከላመነ ሰው የተለየ ሊያደርገው የሚገባው አንድ ነገር ምንድነው?
6. አማኞች አብዛኛውን ጊዜ የከበረውን ተስፋ የሚያስቡት በምን ዓይነት ሰዓት ይመስልሃል? ለምን?
7. አንዳንዴ ሰዎች መከራ ሲደርስባቸው እግዚአብሄር እንደተቆጣባቸው ወይም ደግም ሌሎች ሰዎች ይህንን አይነት አስተሳሰብ ሲሰነዝሩባቸው ይሰማል:: ታዲያ ይህ ክፍል በተለይም ሮሜ ቁ 6-9ና ዕብ 12:7-11 ከዚህ አመለከከት ጋር እንዴት ሊጻረሩ እንደሚችሉ አስረዳ::
8. እስከ ዛሬ በህይወትህ መከራ ሲገጥምህ አቀባበልህ ምን ይመስላል? ዛሬ የተማርከው እውነት ለመከራ ያለህን አመለከከት ምን ያህል ቀይሮታል?

# ጥናት ስምንት (ሮሜ 5:12-21)

የጥናት ዓላማ:- ምን ያህል የእግዚአብሄር ፀጋ ሰፊ እንደሆነ በመመልከት ሥጦታውን የተቀበልነው ሁላችን ፍጻሚያችን በክርስቶስ ከእርሱ ጋራ በህይወት መንገስ እንደሆነ ለመማር::
የምናሰላስለው ጥቅስ: «...በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት አብልጠው በህይወት አይነግሱ::» ሮሜ 5:17

1. ሮሜ 5:12-21 በአንድነት ይነበብ:: ቁ 12-14 ሞት፤ ሃጥያትና ህግን አስመልክቶ የሚናገራቸው እውነቶች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር::
2. ይህ የዛሬው ምንባብ እያንዳንዱ ሰው በየግሉ ቀን ከቀን ስለሚሰራው ሃጥያት እንደማይናገር ልናውቅ የምንችለው እንዴት ነው? ይህንን የማይናገር ከሆነ ታዲያ የሚናገረው ስለየትኛው ሐጥያት ነው?
3. ቁጥር 16 የአዳምን ሃጥያት ውጤትና የእግዚአብሄርን ሥጦታ እያወዳደረ ይናገራል:: ይህ ክፍል ሊናገር የፈለገውን ዋነኛ ሃሳብ በአጭሩ ለመናገር ሞክር::
4. ሞት በሰዎች ሁሉ ላይ ከአዳም የተነሳ እንደነገሰ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሳ ዛሬ ሰዎች ሁሉ በህይወት ነግሰዋል ወይ? ለምን?
5. ቁ18 «በአንድ ሰው መተላለፍ» «በአንዱ የጽድቅ ስራ» የሚሉትን ስናነብ የአንዱ ሰው መተላለፍ ምን እንደሆነ ይታወቃል:: ይህ የአንዱ ሰው የጽድቅ ስራ የሚለው ግን የትኛውን ስራውን አንድ ስራውን ነው የሚናገረው?
6. ቁ 19 በአንዱ ሰው አለመታዘዝና በአንዱ ሰው መታዘዝ ለብዙዎች እንደተረፈ ይናገራል:: ከዚህ ለእኛ የሚሆን ትምህርት ያለ ይመስልሃል ወይ? አለ ከልክ ምን እንደሆነ ተናገር::
7. እንዴት ነው የህግ መምጣት መተላለፍ ወይም ሐጥያት እንዲበዛ ያደረገው? ሐጥያት በበዛበትስ ለምንድነው ጸጋ እንዲበዛ ያስፈለገው (ቁ 20-21)
8. ቁ 15፤17 ትና 20-21 ትን ስታነብ በሶስቱም ጥቅሶች ውስጥ ተደጋግመው የተጠቀሱት ቃላት ምን ምንድናቸው? እነዚሁ ክፍሎች «ተትረፈረፉ» ብለው የሚሏቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር::
9. በክርስቶስ የመንገስህ ሃሳብ ለልብህ ምን ያህል ሃሴትን ያመጣል?

# ጥናት ዘጠኝ (ሮሜ 6:1-14)

የጥናት ዓላማ:- አማኝ ክርስቶስ ሞቶ ሲነሳ እርሱም ለሐጥያት እንደሞተ ለጽድቅ ደግሞ ህያው ሆኖ እንደሚኖር በመረዳት በዚህ እውነት ላይ በመቆም ህይወቱን መምራት እንደሚኖርበት ለመማር:: የምናሰላስለው ጥቅስ: «እንደዚሁም ለሃጥያት እንደሞታችሁ ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሄር ህያዋን እንደሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ::» ሮሜ 6:11

1. ሮሜ 6:1-14 በአንድነት ይነበብ:: በቁጥር 1 ላይ «ጸጋ እንዲበዛ ሐጥያት እየሰራን እንኑር?» ይህ ጥያቄ በመጀመሪያ ደረጃ በዚህ ሥፍራ ለምን ሊጠየቅ ቻለ? በዘመናችንም ጸጋን ተገን አድርገው ሰዎች ወደ ሃጥያት ሊደፋፈሩ ይችላሉ የሚል አስተሳሰብ አለ:: ለዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የሐዋርያው መልስ ምን ነበረ?
2. በቁጥር 3 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የሮሜ ሰዎችን የጠየቃቸው ጥያቄ ምን ነበረ? የዚህን ጥያቄ መልስ ማወቅ ለአማኝ ምን ያህል አስፈላጊ ነው ብለህ ታምናለህ?
3. በቁ 3-4 መሰረት ተጠመቅን እያለ በሚናገረው ሃሳብ የተጠመቅነው ለምንድነው ይላል? ጥምቀት ሲልስ የትኛውን ጥምቀት ማለቱ ነው?
4. «የሞተ ከሃጥያት ነጻ ወጥቷል::» ይህ አባባል ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ:: ቁጥር 7
5. በቁጥር 6 ላይ «ከእንግዲህ የሃጥያት ባሮች እንዳንሆን» ሲል «ከእንግዲህ» የሚለው ቃል የሚጠቁመው የትኛውን ጊዜ ነው?
6. በቁ 11 ላይ «እንደዚሁም» የሚለው ሁለት ሃሳቦችን ማያያዣ ቃል ነው:: ሁለቱ ለማያያዝ የፈለጋቸው ሃሳቦች የትኞቹ እንደሆኑ ገለጽ:: በዚህ ቁጥር ላይ ጸሃፊው ለአንባቢያኑ የሚሰጠው መመሪያ ምንድነው?
7. በቁ12-13 ውስጥ ለአማኞች የተሰጡትን አራት መመሪያዎች ዘርዝር::
8. ቁ12 «እንዲነግስበት» ቁ14 «አይገዛችሁም» እነዚህ ቃላት በምን ላይ ያተኮሩ ናቸው? ይህንን ሲል አማኝ ሃጥያት አይሰራም ማለት ነው ወይ? አስረዳ::
9. ከክርስቶስ ጋራ መሞትና መነሳት የሚለውን ሃሳብ ምን ያህል ተረድተኸዋል? ይህንን እውነት መረዳትህስ ምን ያህል በህይወትህ ላይ ለውጥ አስከትሏል?

# ጥናት አስር (ሮሜ 6:15-23)

የጥናት ዓላማ፡- ከጸጋ በታች መሆን ማለት ለሀጥያት ላይሰንስ የሚሰጥ እንዳልሆነና በዚያ አይነቱ አስተሳሰብ መመላለስ ለሀጥያት ባርነት፤ ለእፍረትና ብሎም መንፈሳዊ ዕድገትን ለሚገድል አኗኗር እንደሚዳርግ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡

1. ሮሜ 6:15-23 በአንድነት ይነበብ፡፡ በ6:1 ላይ የተጠየቀውና በ6:15 ላይ በተጠየቁት ጥያቄዎች መሃል ልዩነት ታያለህ ወይ? ልዩነት የምታይ ከሆነ የጥያቄዎቹ ልዩነት ምን ላይ እንደሆነ አስረዳ፡፡
2. 6:1 «ከቶ አይሆንም» 6:15 «በጭራሽ አይገባም» ብሎ ሳይዘጋው ለምን ያንን ያህል ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አስፈለገው?
3. እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ጥያቄዎችን ሲመልስ ለሁለቱም የጋራ የሆነ አንድ ቃልን ተጠቅሟል፡፡ ይህ ሁለቱንም የሚመለከት የጋራ የሆነው ቃል ምንድነው?
4. ሮሜ 6:1 ላይ የተጠየቀውን ጥያቄ የመለሰው አማኝ ከክርስቶስ ጋራ እንደሞተ በማስረዳት ነው፡፡ በ6:15 ላይ የተጠየቀውን ጥያቄ ስትመለከት መልሱ በምን ላይ ያተኮረ ነው?
5. በቁ 17-18 መሰረት ሰው ነጻ የሚወጣው እንዴት/ምን በማድረግ ነው? በዚህ ክፍል ትምህርት በማለት የጠቀሰው የትኛውን ትምህርት ነው?
6. ቁ 18 «ነጻ ወጥታችሁ የጽድቅ ባሪያዎች ሆናችኋል» ይህ አባባል ስለ የአማኙን ባርነትና ነጻነት በተመለከተ የሚያስተምረን እውነት ምንድነው?
7. «...እየባሰ ለሚሄድ ክፋት ታቀርቡ ነበር» ሀዋርያው ከዚህ አባባሉ ሁልጊዜ በሀጥታችን እየጨመርን እንሄድ እንደነበረ ያስረዳል፡፡ ታዲያ ከጽድቅ አንጻር ይህ አባባል በምን ዓይነት ልንረዳው እንችላለን? ቁ19
8. በዚህ ክፍል ውስጥ የሰፈሩ የሀጥያት ውጤቶች ሆነው በሰው ህይወት ሊከሰቱ የሚችሉ ቢያንስ ሶስት ነገሮች ተናገር፡፡ (ቁ 16፤21፤23)
9. ሐጥያትን በተመለከተ ከዛሬው ትምህርት ምን ተማርክ? በሀጥያት እንዳትኖርና ሀጥያትን እንዳትሰራ የዛሬው ጥናት ምን ያህል አበረታቶሃል?

# ጥናት አስራ አንድ (ሮሜ 7፡1-6)

**የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር የሚቀበለው አገልግሎት ለህግ ሞተን ለክርስቶስ ከሆንን በኋላ ያለውን ማለትም አዲስ በሆነው በመንፈስ መንገድ የምናቀርብለትን አግልግሎት ብቻ እንደሆነ ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡ «ይህም አሮጌ በሆነው በተጻፈው ሕግ ሳይሆን፥ አዲስ በሆነው በመንፈስ መንገድ እንድናገለግል ነው፡፡» ሮሜ 7፡6**

1. ሮሜ 7፡1-6 በቅድሚያ በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁጥር 1-3 ውስጥ ሰፍሮ የሚታየውን መመሪያ ምን እንደሆነ በራስህ ቋንቋ ተናገር፡፡
2. ሕግ በአንድ ሰው ላይ ሥልጣን አለው ሲባል ምን ማለት ነው?
3. በ6፡11 እና በ7፡4 መከከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በማነጻጸር አስረዳ፡፡
4. በዚህ ዛሬ ባነበብነው ክፍል ሮሜ 7፡1-6 መሰረት የሞተው ባላችን ማን ነው? ሁለተኛው ባላችንስ? ለምን ይህንን ለማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
5. ቁ6 «ይህም አሮጌ በሆነው በተጻፈው ህግ ሳይሆን አዲስ በሆነው በመንፈስ መንገድ እንድናገለግል ነው፡፡» ይህንን ሲል ሐዋርያው ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
6. ለህግ ስለመሞታችን ቁ4 ሲናገር ለምንድነው የሞታችሁት ይላል? በክፍሉ መሰረት መቼ ነው ፍሬ እንድናፈራ የሚጠበቅብን?
7. ቁጥር 4ትንና እና ቁ6ትን በአንድነት ስትመለከት እግዚአብሄር ከአማኝ ስለሚፈልገው ነገር ምን ትረዳለህ? እነዚህ ቁጥሮች ለማገልገል ቅድመ ሁኔታ ተደርገው ሊታዩ ስለሚገባቸው ነገሮች የሚናገሩትን ቢያንስ ሁለት ሃሳቦች ተናገር፡፡
8. በእነዚህ ከላይ በተወያያችሁባቸው ሁለት ሃሳቦች አገልግትህን ስትመዝነው ፈተናውን የማታልፍበት አለ ወይ? ዘወትር አገልግሎትህን በእነዚህ መመዘኛዎች መመዘን አትርሳ፡፡

# ጥናት አስራ ሁለት (ሮሜ 7:7-25)

**የጥናት ዓላማ:- ሕግን በመጠበቅ ሰዎች ለመዳን እንደማይችሉ ሁሉ ህግንም በመጠበቅ ለመቀደስ እንደማይችሉ ለመማር::**

**የምናሰላስለው ጥቅስ: «በጎ የሆነውን የማድረግ ምኞት አለኝ፤ ነገር ግን ልፈጽመው አልችልም::» ሮሜ 7:18**

1. ሮሜ 7:7-25 በአንድነት ይነበብ:: በዚህ በተነበበው ክፍል ውስጥ ሃዋርያው የሚጠይቃቸው የተለያዩ ጥያቄዎች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር::
2. ጳውሎስ ለምን ይመስልሃል በህግ ውስጥ ብዙ የተዘረዘሩ ነገሮች እያሉ «አትመኝ» የሚለውን ትዕዛዝ እንደ ምሳሌ ለመጠቀም የፈለገው?
3. በቁ12 ላይ ህጉ ለምን «ቅዱስ» ለምን «ጻድቅ» እና ለምን «መልካም» እንደተባለ እያንዳንዱን በማብራራት ተናገር::
4. ቁ14-18ትን ስታነብ ሐዋርያው ጳውሎስ በህይወቱ የተለማመደውን ችግር ጠቅለል ባለ ሁኔታ ይገልጻል የምትለው አንድ አረፍተ ነገር የትኛው ነው?
5. ገላትያ 5:17 በሮሜ 7:15-17 ከሚገኘው አጠቃላይ ሃሳብ ጋራ በምን መንገድ በሃሳብ እንደሚመሳሰል አስረዳ::
6. ሀዋርያው ከጠየቃቸው ሶስቱ ጥያቄዎች መሃልበአንተ አመለከከት ዋነኛና ጥያቄ የምትለው የትኛው ነው?
7. ይህ ክፍል በአብዛኛው «እኔ» በሚለው ሃሳብ የተሞላ ነው:: ከዚህ አንጻር 8:1-4 ያሉት ቁጥሮች ከዚህ አስተሳሰብ በምን ይለያሉ? እነዚህ ቁጥሮች ለሐዋርያው ጥያቄዎች መልስ እንዴት ሊሆኑ እንደሚችሉ አስረዳ::
8. በቁ24 ላይ የጠየቀውን የሀዋርያውን አይነት ጥያቄ ይዞ ወዳንተ ለሚመጣ ወንድም ወይም እህት ከዚህ አንጻር ምክርህ ምን ይሆናል?

# ጥናት አስራ ሶስት (ሮሜ 8:1-11)

የጥናት ዓላማ:- ከቅድስና ወደ ቅድስና እንድናድግ መንፈስ ቅዱስ ስለተሰጠን የክርስቶስን ህይወት በእኛ ውስጥ እንዲኖር ለእርሱ ስንፈቅድለት ያንጊዜ ህግ የሚጠይቀው ጽድቅ ሁሉ በእኛ ይፈጸማል። የምናሰላስለው ጥቅስ: «ይኸውም በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ በምንመላለስ በእኛ፤ ህጉ የሚጠይቀው ጽድቅ ሙሉ በሙሉ እንዲፈጸም ነው።» ሮሜ 8:4

1. ሮሜ 8:1-11 በአንድነት ይነበብ። ኩነኔን አስመልክቶ ቁጥር 1 የሚመልሳቸውን ሃሳቦች ምን ምንድናቸው? በክርስቶስ ያሉት ከኩነኔ ማምለጥ የቻሉበት ዋነኛው ምክንያት አስረዳ።
2. በቁ1-4 ባለው ክፍል ውስጥ በአማኝና በህግ መሃል ስላለው ግንኙነት የሚናገሩ ቢያንስ ሶስት ነገሮች ተናገር።
3. ሕግ የሚጠይቀው ጽድቅ ሁሉ ሊፈጸም የሚችለው በማን ውስጥ ነው? በሥጋ መመላለስና በመንፈስ መመላለስ ምን ማለት እንደሆነ ሰፋ አርጋችሁ ምሳሌ በመስጠት ተወያዩበት።
4. በቁ5 መሰረት እንደ ስጋ መኖርንና እንደ መንፈስ መኖርን የሚለያቸው ዋነኛ ነገር ምንድነው? ውጤታቸውስ የሚለያየው እንዴት ነው?
5. በቁ5-8 ላይ እያወዳደረ የሚናገራቸው ሁለቱ አይነት ሰዎች አማኝና ያላመነ ወይስ ስጋዊንና መንፈሳዊን ክርስትያን ነው ያወዳደረው? መልስህን አስረዳ።
6. እንደ ስጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሚላቸውን ሰዎች የሚገልጡ በቁ7-8 ላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ዘርዝር።
7. «እናንተ ግን...» በማለት በቁጥር 9 ላይ የሚናገረው እነማንን ነው? በዚሁ ክፍል መሰረት የክርስቶስ ለመሆንና ላለመሆን መለያ ሆኖ የቀረበው ሃሳብ ምንድነው?
8. ቁ9«መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ...» ቁ10«ክርስቶስ በውስጣችሁ ከሆ...» ቁ11«መንፈስ በእናንተ የሚኖር ከሆነ...» የዚህ ዓይነቱ ንግግር የጥርጥር ነገር ነው ወይስ ለምን በዚህ መንገድ ይናገራል?
9. ራስህን ስትመለከት በሥጋ የምትመላለስበት ወይስ በመንፈስ የምትመላለስ ጊዜ ያመዝናል? ዛሬ በዚህ አንጻር የሚረዳህ ሃሳብ የተማርከው ከሆ ለወገኖች አከፍል።

# ጥናት አስራ አራት (ሮሜ 8:12-27)

የጥናት ዓላማ:- ብዙ ጊዜ አማኞች በአብና በወልድ ሥራ ላይ በማተኮር ለመንፈስ ቅዱስ የምንሰጠው ሥፍራ በልሳን ከመናገር፤ ከማጽናናትና ሃይል ከመስጠት ስንወስነው እንገኛለን፤ በዛሬው ጥናት መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወት የሚሰራቸውን ሥራዎች እንማራለን።
የምናሰላስለው ጥቅስ: «እንደገና የፍርሃት ባሪያ የሚያደርጋችሁን መንፈስ ሳይሆን፤ አባ አባት ብለን የምንጠራበትን የልጅነት መንፈስ ተቀብላችኋልና።» ሮሜ 8:15

1. ሮሜ 8:12-27 በአንድነት ይነበብ። በቁ12-17 ውስጥ የተዘረዘሩ መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወት ውስጥ የሚሰራቸው ቢያንስ አራት ነገሮችን ተናገር።
2. እነዚህኑ ቁጥሮች ስናነብ የሚናገረው ለወንድሞች/ለአማኞች እንደሆነ እንረዳለን። ታዲያ በቁ13 ውስጥ ትሞታላችሁ የሚለው ሞት ምን ዓይነት ሞት ነው?
3. «ስለዚህ ወንድሞች ሆይ ግዴታ አለብን»ቁ12 በዚህ ክፍል መሰረት ግዴታ እንዲኖር ያደረገው ነገር ማለትም «ስለዚህ» የተባለለት ነገር ምንድነው?
4. «እንደገና የፍርሃት ባሪያ የሚያደርጋችሁን ሳይሆን... መንፈስ ተቀብላችኋልና፤»ቁ15 ይህ «እንደገና» የሚለው ቃል በዚህ ክፍል ምንን የሚያመለክት ቃል ነው?
5. ሮሜ 8:17-18 በማንበብ መከራን በተመለከተ ልንማር የምንችላቸው እውነቶች ምን ምንድናቸው?
6. መቃተት ሲባል ምን ይገባሃል? በዘሬው ምንባብ ውስጥ ማን ነው እንደሚቃትት የተነገረለት?
7. ቁ23 «ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን...» የሚለው አነጋገር ገና ልጅነታችን የሚረጋገጠው ወደፊት ነው ለማለት ነው ወይስ ምን ማለቱ ነው?
8. በቁ26-27 ላይ የተጠቀሱ መንፈስ ቅዱስ ለአማኝ የሚያደርጋቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? በዛሬው ምንባባችን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወጥ የሚያከናውናቸውን ዋና ዋና ነገሮች ዘርዝር።
9. መንፈስ ቅዱስ በህይወትህ የሰራውና እየሰራ ያለው ድንቅ ሥራ ምን ያህል ተገንዝበሃል? በተራ ቁጥር 8 ከዘረዘርናቸው የመንፈስ ሥራዎች በአንተ አመለከከት ትልቅ ሆኖ የሚታይህ የትኛው ነው? ለምን?

# ጥናት አስራ አምስት (ሮሜ 8:28-39)

የጥናት ዓላማ፡- በሰማይም ሆነ በምድር ወይም ከምድር በታች አማኝን አጥብቆ ከያዘው ከሃይለኛው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየው የሚችል አንዳችም ነገር እንደሌለ ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ: «ይህንን ተረድቻለሁ፤...የትኛውም ፍጥረት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም፡፡» ሮሜ 8:39

1. በቁ28 ላይ ነገር ሁሉ ለበጎ ይደረግላቸዋል የሚላቸው እነማን ናቸው? «ነገር ሁሉ» የሚለው አነጋገር ውስጥ የማይጠቃለሉ ነገሮችስ አሉ ወይ? አስረዳ
2. አማኝን በተመለከተ የእግዚአብሄር ውሳኔ ምንድነው? (ቁ29-29) በዚህ ክፍል መሰረት ይህንን ውሳኔውን በሥራ ለመተርጎም የወሰዳቸውን እርምጃዎች በየተራ ዘርዝር፡፡
3. «ጠራቸው፤ አጸደቃቸውና አከበራቸው የሚሉት ሶስቱም የሃላፊ ጊዜን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ከዚህ አነጋገር ስለ አማኝ የደህንነት ሁኔታ ምን የምታየው እውነት አለ?
4. በቁ31-34 ውስጥ ሐዋርያው የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች ዘርዝር፡፡ በቁጥር 31 ላይ «ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን?» በማለት «ለዚህ» የሚለውን ቃል ሲጠቀም ከየትኛው ሃሳብ ጋራ ሊያያይዝ ፈልጎ ይመስልሃል?
5. «እግዚአብሄር ከእኛ ጋራ ከሆነ ማን ይቃወመናል?» ሲል ተቃዋሚ የለንም ማለት ነው ወይ?
6. ቁ23 እኛ እንማልዳለን፤ ቁ26 መንፈስ ቅዱስ ይማልድልናል፤ ቁ34 ኢየሱስ ይማልድልናል፡፡ ይህ ሁሉ ምልጃ እየተከሄደ ለምንድነው ተመልሶ በቁ35-36 ስለመከራና ችግር የሚያወራው?
7. በቁ35-37 ላይ በዋነኛነት የቀረበው ጥያቄ ምንድነው? ለጥያቄው በመልስነት የቀረበው ሃሳብስ ምንድነው? በክፍሉ በዝርዝር ከተቀመጡት ነገሮች ውጭ ልትጨምር የምታስበው ነገር ከለ?
8. በቁ38-39 መሰረት ጳውሎስ ተረዳሁ የሚለው አንድ እውነት ምንድነው? በዚህ ክፍል የተዘረዘሩትን ነገሮች በቁ37-38 ከተዘረዘሩት ጋራ በማነጻጸር አላቸው የምታየውን ልዩነት ወይም አንድነት ተናገር፡፡
9. ከእግዚአብሄር ፍቅር ይለየኛል ብለህ የምትፈራው ነገር ኖሮህ ያውቃል ወይ? ከሆነስ የዛሬው ትምህርት ምን ያህል ጠቃሚ ሆኖ እንዳገኘኸው ለወገኖች አከፍል፡፡

# ሮሜ አጋማሽ ማጠቃለያ ጥናት

# ጥናት አስራ ስድስት (ሮሜ 1፡1-8፡-39)

1. የመጽሃፍ ቅዱስ አዋቂዎች ሮሜ 1፡17 «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» የሚለው ጥቅስ የሮሜን መጽሃፍ ሃሳብ ያጠቃልላል ብለው ይናገራሉ፡፡ ይህ የተባለበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
2. ሮሜ 3፡25-26 ኢየሱስን መስዋዕት አድርጎ ያቀረበው የራሱን ጽድቁን ለማሳየት ነው ይላል፡፡ በክርስቶስ መስዋዕትነት የእግዚአብሄር ጽድቅ ሊታይ የሚችለው እንዴት ነው?
3. በሮሜ ምዕራፍ አራት ውስጥ የአብርሃምን ህይወት ጳውሎስ እያብራራ ላለው ሃሳብ መደገፊያ በምን መንገድ ነው የተጠቀመበት?
4. ሮሜ 5፡1-5 ባለው ክፍል ውስጥ በእምነት የመጽደቃችን ውጤቶች ሆነው የተጠቀሱ ቢያንስ ሶስት ነገሮችን ዘርዝር፡፡
5. ምዕራፍ 6 ጸጋ በዛ ማለት በሃጥያት መኖር ማለት እንዳልሆነ የሚናገር ክፍል ነው፡፡ ቁ3፤ 11 አና 13ትን በማንበብ አማኝ በህይወቱ በሃጥያት ላለመኖር ሊወስዳቸው የሚገባውን ሶስት እርምጃዎች ተናገር፡፡
6. በሮሜ 6፡15 ላይ የሚታየው ዓይነት አመለከከት ባለው ሰውና በሮሜ 7፡18 ላይ በምታየው ሰው መከከል ምን ልዩነት ታያለህ? የእነዚህ ሁለት ሰዎች ችግር ምን እንደሆነ አስረዳ፡፡
7. በምዕራፍ ሰባት ላይ ለሚታየው ሰው ችግር በምን መንገድ ነው ምዕራፍ ስምንት መልስ ሊሆን የሚችለው?
8. ሮሜ ምዕራፍ 8ትን ስንመለከት አጨራረሱ አስደናቂና በተስፋ እንድንሞላ የሚያደርገን ነው፡፡ ይህ ግሩም የሆነ ምዕ 8 የተጠቃለለበት ሃሳብ የተባለው ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
9. ከዛሬው ትምህርት ለህይወትህ የቀረልህን/ሽን ነገር ለወገኖች አከፍል/ፍይ፡፡

# የሮሜ መጽሐፍ (18ለ)

## ጥናት አስራ ሰባት(ሮሜ 9፡1-13)

የጥናት ዓላማ፡ የተስፋ ቃል አለን ከማለታችን አስቀድመን የተስፋ ቃሉ ምን ማለት ነው  ለማንስ ነው ቃል ኪዳኑ የተገባው ብለን መጠየቅ እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ነገር ግን የእግዚአብሄር ቃል ተሸሯል ማለት አይደለም፤ ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ እስራኤል አይደለምና፡፡›› ሮሜ 9፡6

1. ሐዋርያው ምዕራፍ ስምንትን በጨረሰበት ስሜትና ምዕራፍ ዘጠኝን በጀመረበት ስሜት መሃል ግልጽ ሆኖ የሚታይ ልዩነት አለ፡፡ ይህ የስሜት ልዩነት ምን እንደሆነ አስረዳ፡፡
2. ቁ1-3ትን ስታነብ በጳውሎስ ህይወት ግልጽ ሆኖ የሚታይህ አንድ ነገር ምንድነው? በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ልክ እንደ ጳውሎስ  ስሜቱን ለእግዚአብሄር የገለጠ ሌላ ሰው ማን ነው?
3. የእስራኤልን ህዝብ ከሌሎች አህዛብ ይልቅ የታደሉ የሚያደርጓቸው በቁ1-5 ላይ ጳውሎስ የዘረዘራቸው ሰባት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
4. በቁ6 ላይ የእግዚአብሄር ቃል አልተሸረም ሲል ለዚህ የሰጠው ምክንያት ምንድነው? ይህንን ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ፡፡
5. በቁ6-13 ውስጥ ሐዋርያው የእግዚአብሄር ቃል እንዳልተሻረ ለማስረዳት የተጠቀመባቸው ሁለት ምሳሌዎች ምን ምንድናቸው? በምሳሌዎቹ ውስጥ የምንመለከተው ለሁለቱም የጋራ የሆነ አንድ ሃሳብ ምንድነው?
6. በእስማኤልና በይስሃቅ ከተሰጠው ምሳሌ ይልቅ በኤሳውና በያዕቆብ የተሰጠው ምሳሌ የበለጠ ጠንካራ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው በምን መንገድ ነው?
7. ቁ13 ላይ «ያዕቆብን ወደድሁ፤ ኤሳውን ግን ጠላሁ» ይህ አባባል እግዚአብሄር ሰውን ይጠላል ማለት ነው ወይ? ይህ ከሆነስ እግዚአብሄር ፍቅር እንደሆነ ከሚናገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ጋራ እንዴት ይታረቃል?
8. ዛሬ በተነበበው ክፍል ሐዋርያው ሊያስረዳን የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ ምንድነው ትላለህ? ክፍሉ የሚናገረው ስለ እስራኤል ህዝብ ከሆነ ለእኛ ሊኖረው የሚችለው መልእክትስ ምንድነው?

# ጥናት አስራ ስምንት (ሮሜ 9፡14-23)

የጥናት ዓላማ፡ እግዚአብሄር የፈቀደውን ነገር ለማድረግ ሰውን ማማከር እንደሌለበትና የወደደውን ለማድረግ ችሎታ ብቻ ሳይሆን መብትም እንዳለው ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ስለዚህ እግዚአብሄር ሊምረው ለሚወደው ምህረት ያደርግለታል ልቡ እንዲደነድን የፈለገውንም ያደነድነዋል፡፡›› ሮሜ 9፡18

1. ሮሜ 9፡14-23 በአንድነት ይነበብ፡፡ ይህንን ክፍል ስታነብ ወደ አዕምሮህ የመጣ ጥያቄ አለወይ? ጥያቄህ በክፍሉ ውስጥ ከተጠየቁት ጋራ ተመሳሳይነት እንዳለው አወዳድሩ፡፡
2. በዚህ ክፍል የምናያቸውን የእግዚአብሄርን የተለያዩ ባህርያት ዘርዝር፡፡ ከሌሎቹ ሁሉ ጎልቶ የምታየው ባህርይ የትኛው እንደሆነ ተናገር፡፡
3. በቁ 14 እና 19ን በጠየቁት ሰዎች ዓይነት ምን ልዩነት ይታይሃል? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ ተናገር፡፡
4. የሙሴንና የፈርዖንን ህይወት በማነጻጸር የእግዚአብሄርን ምህረት በተመለከተ ልንማር የምንችለውን እውነት አስረዳ፡፡
5. በቁ19 ላይ የሚገኘውን ጥያቄ በራስህ አማርኛ ጠይቅ፡፡ ይህ ሰው ለጠየቀው ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ አግኝቷል ወይ? የተሰጠውን መልስ በአጭሩ ከሶስት ባልበለጡ ቃላት ተናገር፡፡
6. ሮሜ 9፡14-23 ያለው ክፍል ሊያስተምረን የፈለገው አንድ እውነት አለ ቢባል ይህ እውነት ምንድነው ትላለህ?
7. የእግዚአብሄር ሉዓላዊ አሰራር ጥያቄ ሆኖብህ ያውቃል ወይ? ይህ ጥናት ለጥያቄህ ምላሽ የሆነልህ በምን መንገድ እንደሆነ ለወገኖች አካፍል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥያቄ ሲመጣብህ እኛ ሰዎች እርሱ እግዚአብሄር መሆኑን አትዘንጋ፡፡

# ጥናት አስራ ዘጠኝ (ሮሜ 9፡23-33)

የጥናት ዓላማ፡ ጽድቁን ለማግኘት ሳንሯሯጥ፤ ህዝቡ ሳንሆን ህዝቤ፤ የተወደድን ሳንሆን የተወደዳችሁ ያለንን እግዚአብሄርን ምን ያህል ልናመሰግነው እንደሚገባን ለማየት፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ህዝቤ ያልሆኑትን ህዝቤ ብዬ እጠራለሁ፤ ያልተወደደችውንም የተወደደችው ብዬ እጠራለሁ፡፡›› ሮሜ 9፡25

1. ሮሜ 9፡23-33 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ 23-24 ተጠሩ የሚላቸው እነማንን ነው? ስለጠራበት ምክንያትስ ይህ ክፍል የሚነግረን ነገር ምንድነው?
2. ቁጥር 25-26 የሚናገረው ስለማን ነው? ይህ ክፍል ምን ለማለት እንደፈለገ አስረዳ፡፡
3. በቁጥር 27-29 ያለው ክፍል ዋና ሃሳብ ምንድነው?
4. በሮሜ 9፡16 የተነገረውን ነገር በቁጥር 30-31 ከሰፈረው ሃሳብ ጋራ በማነጻጸር ጽድቅ ማግኘትን በተመለከተ ምን ሃሳብ ይሰጠናል?
5. በቁ30-31 ውስጥ የምናያቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች ማንና ማን ናቸው? በእነዚህ ሰዎች መሃል የምታያቸውን ልዩነቶች ዘርዝረህ ተናገር፡፡
6. የእግዚአብሄርን ምርጫ አስረግጦ በሚናገር በዚህ ክፍል ውስጥ ቁጥር 30-33 የሰውን ሃላፊነት በጥቂቱም ቢሆን የሚጠቁመን የትኛው ሃሳብ ነው?
7. በምን መንገድ ይመስልሃል ይህ ክፍል ከሌላው ምዕ 9 ላይ ከሰፈረው ሃሳብ ጋራ ሊያየዝ የሚችለው?
8. ከእግዚአብሄር ሉዓላዊ ምርጫ የተነሳ የእግዚአብሄር ህዝብ መባልህና በእግዚአብሄር የተወደድክ መሆንህ በልብህ የሚያመጣው ስሜት ምንድነው? ሳምንቱን በዚህ ሃሳብ ጌታን በልብህ ቀድሰው፡፡

# ጥናት ሃያ (ሮሜ 10፡1-8)

የጥናት ዓላማ፡ ለዘመዶቻችንም ሆነ ለአገራችን ምኞትና ፀሎታችን ከማናቸውም ነገር በላይ በቅድሚያ በነፍሳቸው ደህንነት ላይ ያተኮረ ሊሆን እንደሚገባው ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ወንድሞች ሆይ ስለ እስራኤላውያን የልቤ ምኞት፣ እግዚአብሄርንም የምለምነው እንዲድኑ ነው፡፡›› ሮሜ 10፡1

1. ሮሜ 10፡1-13 በአንድነት ይነበብ፡፡ ሐዋርያው ስለ እስራኤላውያን በቁጥር 1 ላይ የሚናገረው ምን እንደሆነ በራስህ አባባል ግለጽ፡፡ ከመመኘት አልፎ የሚያደርገው ነገር ምንድነው?
2. ምዕራፍ 9 እግዚአብሄር የመረጣቸው ብቻ እንደሚድኑ አስተምሮ በዚህ ክፍል ደግሞ እንዲድኑ መፀለዩ ምን ይነግረናል?
3. ጳውሎስ በቁ2 ላይ አይሁድ ለእግዚአብሄር ስላላቸው ቅናት መመስከር እችላለሁ የሚያሰኘው ምንድነው ትላለህ? በተለይ ፊሊጵስዩስ ምዕራፍ ሶስትን መመልከት ይረዳል፡፡
4. ስለ ቅንዓታቸው ሌላ በዚሁ ቁጥር ውስጥ የሚናገረው ነገር ምንድነው? ያለ እውቀት የሆነ ቅንዓት የሚለውን ሃሳብ ከእኛ ህዝብ ጋራ በማገናዘብ አስረዳ፡፡ ምሳሌ 19፡2
5. አይሁድ ለእግዚአብሄር ጽድቅ ለመገዛት ያልቻሉበት ምክንያት ለምንድነው?
6. በቁ5-6 ውስጥ ስንት ዓይነት የጽድቅ አይነቶች እናያለን? አነዚህ ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡
7. በሁለቱ የጽድቅ መንገዶች መሃል ስላለው ልዩነት ቁ5-8 ምን ያሳየናል? በተለይ ቁ6-7 ያለው ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ፡፡
8. በቀደምተኛነት ለወገኖችህ የምትመኘውና የምትፀልየው ምን እንዲሆንላቸው ነው? ይህንን ጥናት ማጥናትህ ምኞትህንና ጸሎትህን የሚቀይረው በምን መንገድ ሊቀየር እንደምትወድ ወገኖችህ አካፍል፡፡

# ጥናት ሃያ አንድ (ሮሜ 10፡9-21)

የጥናት ዓላማ፡ ሰዎች የጌታን ስም ጠርተው ይድኑ ዘንድ ወንጌል መስማት እንደሚያስፈልጋቸውና የማስማቱንም ሃላፊነት አስቀድመው ወንገልን ሰምተው በተቀበሉት ላይ አደራ እንደተጣለ ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና፡፡ ታዲያ ያላመኑትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ስለ እርሱስ ሳይሰሙ እንዴት ያምኑበታል?...›› ሮሜ 10፡13-14

1. ቁጥር 9-12 ያለው ክፍል ደህንነትን በተመለከተ የሚያስተምረንን እውነቶች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡ ላላመነ ሰው ለመመስከር ይህንን ክፍል በምን መንገድ ልትጠቀምበት እንደምትችል አስረዳ፡፡
2. ቁ9 ላይ ‹‹ኢየሱስ ጌታ ነው ብለህ በአፍህ ብትመሰክር… ትድናለህ›› ይላል ይህ በአፍ መመስከር ማለት ምን ማለት ነው? ለምንድነው ይመስልሃል ትልቅ ሥፍራ የተሰጠው?
3. ‹‹የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል›› ቁ13 ሲል ‹‹ኢየሱስ›› ያለ ሁሉ መንግስተ ሰማያትን ይወርሳል ማለቱ ነው ወይ? ያ ካልሆነ እንግዲያስ ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ፡፡
4. ቁ13-16 የምናነበው ክፍል ወንጌልን በተመለከተ የሚናገራቸውን ቢያንስ ሰባት እውነቶች በመዘርዘር አስረዳ፡፡
5. በቁ13-16 የተዘረዘሩት ነገሮች ለእያንዳንዱ አማኝ የሚያስተጋቡት የጥሪ መልዕክት ምንድነው ብለህ ታምናለህ? አንድ በአንድ በመዘርዘር ሰፋ አድርጋችሁ ተወያዩባቸው፡፡
6. ምዕራፍ ዘጠኝ ከሚናገረው ከእግዚአብሄር ሉዓላዊነት ጋራ ይህ ክፍል እንዴት አብሮ ማስኬድ እንደሚቻል ተናገር፡፡
7. የዛሬው ምንባብ የወንጌልን ስርጭት በተመለከተ የሚያበረታታህ በምን መንገድ ነው?

# ጥናት ሃያ ሁለት (ሮሜ 11፡1-15)

የጥናት ዓላማ፡ እግዚአብሄር እኛ እንድናደርግለት የጠራንን ነገር ለማከናወን ባንወድ በእኛ በረከቱ ይቀርብናል እንጂ አርሱ የገባውን የተስፋ ቃል የሚፈጽምበት መንገድ እንደማያጣ ለማስገንዘብ።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ነገር ግን የእነርሱ መተላለፍ ለዓለም በረከት ከሆነ፤ ውድቀታቸውም ለአህዛብ በረከት ከሆነ፤ ሙላታቸው ምን ያህል ታላቅ በረከት ያመጣ ይሆን?›› ሮሜ 11፡12

1. ሮሜ 11፡1-15 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። በቁጥር 1-4 ውስጥ እግዚአብሄር ህዝቡን እንዳልጣላቸው ፀሐፊው የሚሰጣቸው መረጃዎች ምን ምንድናቸው?
2. እግዚአብሄርን የሚያመልክን ሰው በተመለከተ በኤልያስና በእግዚአብሄር አመለካከት መሃከል ምን ልዩነት ታያለህ? ከዚህ ምን የምትማረው ነገር ይኖራል?
3. በቁጥር 1እና በቁጥር 11 ላይ በተጠየቁት ጥያቄዎች መካከል ልዩነት ታያለህ ወይ? መልስህን አብራራ።
4. በቁ11-12 እግዚአብሄር እስራኤልን ወደራሱ ለመመለስ የተጠቀመበት ምን መንገድ ታያለህ? የዚህ ዓይነቱን መንገድ መጠቀሙ እስራኤላውያንን እንዴት ወደ እግዚአብሄር ሊመልሳቸው ይችላል ብለህ ታምናለህ?
5. በቁጥር 11እና በቁ14 መሃል አንድ የጋራ የሆነ ሃሳብ አለ። ይህ የጋራ የሆነው ሃሳብ ምንድነው?
6. ቁ13-14 ያለውን ክፍል ስታነብ የሐዋርያው ጳውሎስ አሰራር በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደመግደል ሆኖ ሊቆጠር የሚችለው እንዴት ነው?
7. እስራኤል እግዚአብሄር ወዳሰበላቸው ሥፍራ የመመለሳቸው ተስፋ በቁ12ት እና በቁ15 መሰረት ለጳውሎስ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?
8. ‹‹የእነርሱ መተላለፍ ለዓለም በረከት ከሆነ…›› እግዚአብሄር ለአብርሃም በአንተ አህዛብ ይባረካሉ ሲል በዚህ መንገድ ይመስልሃል ወይ? በአንተ መታዘዝ ሊሰራ ያለውን ነገር ባትታዘዝ ሊያደርግ ስለሚችለው ነገር ከዚህ ክፍል ምን እንደተማርክ ለወገኖች አካፍል።

# ጥናት ሃያ ሶስት (ሮሜ 11፡16-36)

የጥናት ዓላማ፡ የሆንነውን የሆንነው ከእግዚአብሄር ቸርነት የተነሳ እንጂ ከሌሎች የተሸልህ ሀነን ስለተገኘን ስላልሆነ ልባችን የትዕቢትን ነገር እንዳያስብ ልንጠነቀቅ እንደሚገባን ለማሳሰብ።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹… ትክክል ነው፤ እነርሱ የተሰበሩት ካለማመን የተነሳ ነው፤ አንተም በእምነት ቆመሃል፤ ፍራ እንጂ ትዕቢተኛ አትሁን።፡››

1. ሮሜ 11፡16-36 በአንድነት ይነበብ። ከዘኍ 15፡19-21 ጋራ በማገናዘብ ሮሜ 11፡16 ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ።
2. ቁ17 ላይ አንተ እያለ የሚናገረው ለማን ነው? ይህ ቁጥር ስለ አህዛብ የሚናገራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
3. በቁ18 ላይ ‹‹አንተ ሥሩን አትሸከምም፤ ሥሩ ግን አንተን ይሸከምሃል እንጂ።፡›› በዚህ ክፍል ሥር በመባል የተነገረለት ማን ነው? እኛንስ የሚሸከመው በምን መንገድ ነው?
4. ሮሜ 11፡19-21 እስራኤላውያን ስላሉበት ሁኔታ ምን ያስረዳናል? ስለ አህዛብስ?
5. ቁ16-24ትን አንብበህ በአንድ አጭር አረፍተ ነገር አጠቃል ብትባል ምን ትላለህ?
6. በቁ 25 ላይ ምስጢር በመባል የተነገረው ነገር ምንድነው? ይህንን ምስጢር መረዳት ለአህዛብ ጠቃሚ የሚሆው በምን መንገድ ነው?
7. በቁ 28 ላየ ወንጌልን በተመለከተና ምርጫን በተመለከተ ብሎ የሚናገረውን ሃሳብ በራስህ ቃል ምን ለማለት እንደፈለገ አስረዳ። ‹‹የእግዚአብሄር ስጦታና ጥሪ ጸጸት የለበትም›› የሚለው ቃል በልብህ ምን ዓይነት ስሜትን ያመጣል?
8. በቁ33-36 ባለው ክፍል ጳውሎስ በውስጡ የሚመላለሰው ስሜት ምን ይመስልሃል? በሮሜ 1፡1-11፡36 ካጠናናቸው ነገሮች ውስጥ ወደዚህ ዓይነት ስሜት ሊያስገቡ ከሚችሉት ጥቂቶቹን ሃሳቦች ለወገኖች ተናገር።

# ጥናት ሃያ አራት (ሮሜ 9፡1-11፡36)

## ማጠቃለያ ጥናት

የጥናት ዓላማ፡ በሮሜ ምዕራፍ 9-11 ውስጥ የተማርናቸውን ዋና ዋና እውነቶች ለማስታወስና ሶስቱ ምዕራፎቹ እንዴት እንደሚያያዙ ለመመልከት፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹የእግዚአብሄር የጥበቡና የእውቀቱ ባለጠግነት አይመረመርም፤ ለመንገዱም ፈለግ የለውም!›› ሮሜ 11፡33

1. እግዚአብሄር ህዝቤ ላላቸው ለአይሁድ በአብርሃም በኩል የገባውን የተስፋ ቃል ሽሯል ወይ? ብለው ለሚጠይቁ ሰዎች የጳውሎስ መልሱ ምንድነው? ይህንን እውነት ያስረዳው በምን መንገድ እንደነበረ 9፡6-15ትን በማንበብ አስረዳ፡፡
2. በሮሜ 9፡9-26 ውስጥ በቀጥተኛና በማያወላውል መንገድ የእግዚአብሄርን ሉዓላዊነት ያስተምራል የምትለው የትኛው ጥቅስ እንደሆነ ተናገር፡፡ ለምን?
3. የሰው ልጆችን ደህንነት በተመለከተ፤ በምዕ 10 የምናነበው ክፍል በምዕ 9 ከሰፈረው የእግዚአብሄርን ሉዓላዊነት ሃሳብ ጋራ እንዴት እንደሚሰራ ተናገር፡፡
4. ሮሜ 10፡18-11፡6 ትን በማንበብ የእግዚአብሄርን አሰራር በተመለከተ ሊያስተምረን ያለው አንድ እውነት በአንተ አመለካከት ምንድነው ትላለህ? ይህንን ለማስረዳት የተጠቀመባቸው ምሳሌዎች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
5. ሮሜ 11፡13-32 ያለው ክፍል እኛ አህዛቦች ስለ እስራኤላውያን ሊኖረን ስለሚገባን አስተሳሰብ ምን ታያለህ? እግዚአብሄር እስራኤልን ጥሏቸዋል ብለን የምናምን ከሆነ ይህ አመለካከት በቁ 21 መሰረት አደገኛ የሚሆነው ለምንድነው?
6. ሮሜ ምዕራፍ 9-11 ያለው ክፍል ዋና ዋና ሃሳቦቹ ምን ምን እንደሆኑና የምዕራፎቹ ሃሳብ እንዴት እንደሚያያዝ አጠር ባለ መልኩ ተናገር፡፡

# የሮሜ መጽሐፍ (18ሐ)

## ጥናት ሃያ አምስት (ሮሜ 12፡1-8)

የጥናት ዓላማ፡ አማኝ ይንንን ዓለም ላለመምሰልና የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለማወቅ ከፈለገ በአዕምሮ መታደስ መለወጥ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ እንድንረዳ ሁላችንንም ለማሳሰብ።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹…የእግዚአብሄር ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአዕምሯችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ።›› ሮሜ 12፡2

1. ሮሜ 12፡1-8 ያለው በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ባለው ክፍል ውስጥ ጳውሎስ እያነጋገረ ያለው ማንን ነው? እነዚህን ሰዎች ምን እንዲያደርጉ ነው የሚያደፋፍራቸው? የእግዚአብሄር ርህራሄ በመባል የተጠቀሰው ነገር የሚናገረው ስለየትኛው ርህራሄነው?
2. በቁ 1 ላይ ስለተጠቀሰው የመስዋዕት ዓይነት የተረዳሃቸውን ግንዛቤዎች በሙሉ አስፍር። ይህ መስዋዕት በብሉይ ኪዳን ከምናያቸው መስዋዕቶች የሚለየው በምን መንገድ ነው?
3. በቁ2 መሰረት በአዕምሮአችሁ መታደስ መለወጣችን የሚጠቅመው ለምንድነው? ‹‹ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ…›› ሲል የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለማወቅ እኛ ስላለብን ሃላፊነት ምን ያስተምረናል?
4. በቁጥር 2 ላይ የተሰጠው መመሪያ በቁ3 ላይ ለተሰጠው ትዕዛዝ ጠቃሚ ሆኖ የሚገኘው በምን መንገድ ነው ትላለህ?
5. የዛሬው ምንባብ ስለ ስጋዊ አካላታችን የሚነግረን ሁለት እውነቶች ምንና ምንድናቸው? ይህንን እውነት በምን መንገድ ነው ለመንፈሳዊ አካል ምሳሌ እንደሚሆን የሚያስተምረው?
6. ቁ6-8 ባሉት ቁጥሮች ስጦታን በተመለከተ የምታያቸውን ቢያንስ ሶስት እውነቶች ዘርዝር።
7. በአዕምሮ መታደስ በተቀሩት ምዕራፎች ውስጥ ለምንማራቸው ሃሳቦች በሙሉ መሰረት ነው በሚለው ሃሳብ ምን ያህል ትስማማለህ? ለምን ይህንን ለማለት እንደቻልክ አስረዳ።
8. ፈቃዱን ለማወቅና በአዕምሮህ ለመታደስ ምን ያህል በእግዚአብሄርን ቃል ራስህን ትሞላለህ?

# ጥናት ሃያ ስድስት (ሮሜ 12፡9-21)

የጥናት ዓላማ፡ ጌታን እንድናገለግል ብቻ ሳይሆን አገልግሎታችንን በትጋትና በጋለ/በተነቃቃ መንፈስ እንድናገለግል እንደሚጠበቅብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ጌታን ለማገልገል በመንፈስ የጋላችሁ ሁኑ እንጂ ከዚህ ትጋት ወደ ኋላ አትበሉ።›› ሮሜ 12፡11

1. ሮሜ 12፡9-21 በአንድነት ይነበብ። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ 8፡8-11 የሚናገረው ሃሳብ በዚህ በሮሜ 12፡9 ‹‹ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን፤›› ከሚለው ሃሳብ ጋራ በማነጻጸር ተናገር።
2. በቁ10 እና 16 ላይ እርስ በእርሳችን እንድናደርግ የታዘዝናቸው ሶስቱ ነገሮች ምን ምንድናቸው? ከእነዚህ ከሶስቱ ውስጥ በበለጠ ስንቸገርበት የሚታየው በአንተ አስተያየት የትኛው ትዕዛዝ ይመስልሃል?
3. መዋደድ፤ መከባበርና መስማማት የሚሉት ትዕዛዞችን ለመፈጸም አንድ መሟላት የሚኖርበት ነገር አለ። ይህ መሟላት ያሚኖርበት ቅድመ ሁኔታ ምንድነው?
4. ሐዋርያው በቁ11 ላይ ክርስትያኖችን የሚያበረታታቸው ምን ምን እንዲያደርጉ?
5. በቁ12 ላይ የተዘረዘሩት ሶስት ነገሮች ጌታን ለማገልገል ካለን ግለት እንዳንቀዘቅዝና ወደኋላ እንዳንል እንዴት ሊረዱን ሊረዱን የሚችሉት በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ።
6. በቁ13 ላይ የተሰጡን ሁለት ትዕዛዞች ምንና ምንድናቸው? በእነዚህ በሁለት ትዕዛዞች መሃል የምትረዳው ልዩነት ምንድነው? የትኛው የሚቀል ይመስልሃል?
7. በቁ21 ‹‹ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።›› ይህ ትዕዛዝ ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ።
8. በቁ11 ላይ ጌታን ስለማገልገል የምናነበው ሃሳብ የግለትንና የትጋትን ጥያቄ እንጂ የማገልገልና ያለማገልገል ጥያቄ የለውም። በጌታ አገልግሎት ምን ያህል ተሳትፎ አለህ? እያገለገልክ ከሆነ አገልግሎትህን ምን ያህል በትጋትና በጋለ መንፈስ ትሰራለህ? ዛሬ የተማርከው ትምህርት ለወደፊቱ በትጋትና በመነቃቃት እንድታገለግል ጠቅሞህ ከሆነ ለወገኖች አካፍል።

# ጥናት ሃያ ሰባት (ሮሜ 13፡1-7)

የጥናት ዓላማ፡ እግዚአብሄር የቤተሰብንና የቤተ ክርስትያንን መሪዎች ብቻ ሳይሆን የመንግሥት ባለሥልጣናትም ጭምር በእግዚአብሄር የተሾሙ ስለሆኑ መገዛት እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ማንም ሰው በሥልጣን ላሉት ሹማምንት መገዛት ይገባዋል፤ ከእግዚአብሄር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለምና፤›› ሮሜ 13፡1

1. ሮሜ 12፡17-21 ለተዘረዘሩት እንዳንበቀል ለተነገረን ዓይነት ሰዎች እግዚአብሄር በምን ዓይነት ነው በዚህ በሮሜ 13፡1-4 መልስ ሲሰጥ የምናየው?
2. ቁ1-2 ያለው ክፍል ስለ ሥልጣን የሚያስተምራቸው ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡
3. ባለሥልጣንን ሳንፈራ በድፍረት አንገታችንን ቀና አድርገን መሄድ ከፈለግን ማድረግ ያለብን ይህ ክፍል የሚነግረን አንድ እውነት ምንድነው?
4. በቁጥር 3 እና 4 መሰረት እግዚአብሄር ከመልካም ባለስልጣናት የሚጠብቃቸው ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ምን ምንድናቸው?
5. በቁ 4 እና 6 ውስጥ ለእነዚህ ባለሥልጣኖች የተሰጣቸው ስም ምንድነው? እኛ አገልግሎት ብለን ከምንለው ይህ የእነርሱ አገልግሎት በምን መንገድ ይለያል?
6. ይህ ምንባብ ሰዎች ለባለሥልጣናት ለመገዛት የሚችሉባቸው ስንት መንገዶችን ይጠቁመናል? እነዚህ ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ የትኛውን መንገድ እንድንከተል ነው የሚያደፋፍረን?
7. ለባለሥልጣናት ከመገዛት ሌላ ከእነርሱ ጋራ በተገናኘ ልናደርግ ስለሚገቡን ነገሮች ቁጥር 6 እና 7 ምን ያስተምሩናል?
8. ኤፌ 5፡22፤ ዕብ 13፡17 እና ሮሜ 13፡1 እነዚህ ሶስት ጥቅሶች የሚመሳሰሉባቸው የጋራ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
9. ‹‹መገዛት›› የሚለውን ሃሳብ በተራ ቁ8 ከተዘረዘሩት ሶስቱ ተቋማት ውስጥ በየትኛው ተቋም አስቸጋሪ ሆኖ አግኝተኸዋል? ዛሬ በተማርከው ትምህርት የተነሳ የነገ አኗኗርህን ለመቀየር የወሰንክበት ነገር ካለ በምን መልኩ ለመቀየር እንዳሰብክ ለወገኖች አካፍል፡፡

# ጥናት ሃያ ስምንት (ሮሜ 13፡8-14)

የጥናት ዓላማ፡ ዕለት ዕለት ኑሯችንን ስንኖር በሰዎች ሁሉ ላይ መክፈል ያለበት የፍቅር ዕዳ እንዳለብን ሰዎች መመላለስ እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እርስ በእርሳችሁ ከመዋደድ በቀር የማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፤ ባልንጀራውን የሚወድ እርሱ ሕግን ፈጽሟልና፡፡›› ሮሜ 13፡8-14

1. ሮሜ 13፡8-14 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ8 ላይ ዕዳን አስመልክቶ የተጠቀሱት ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
2. ‹‹እርስ በእርሳችሁ ከመዋደድ በቀር የማንም ዕዳ አይኑርባችሁ›› ከዚህ ክፍል ከምትረዳው የፍቅር ዕዳ ያለበት ማን ነው? እንዲወድ የታዘዘውስ ማንን ነው? ለምን ይህንን ልትል እንደቻክ አስረዳ፡፡
3. ፍቅር የህግ ፍፃሜ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ለምንድነው?
4. ቁ11 ላይ ‹‹ዘመኑን በማስተዋል ይህንን አድረጉ›› በዚህ ክፍል ‹ይህንን› የሚለው ቃል የሚጠቁመው/የሚያመለክተው የትኛውን ሃሳብ ነው?
5. በቁ11-12 መሰረት ዘመኑን አስተዋለ የሚባል ሰው መረዳት የሚገባው ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር፡፡
6. የፍቅር ዕዳን እንደሚከፍል ሆኖ ለመኖር ውሳኔ ያደረገ ሰው በህይወቱ መቀየር ስለሚኖርበት ነገሮች በቁ12-14 ምን ይናገራል?
7. ቁ14 ላይ ለሥጋ አታስቡ ሲል መብላት፤ መጠጣት፤ ሰውነትን ማሳረፍና የመሳሰሉት ነገሮች አያስፈልጉም ለማለት ነው ወይስ ያ ማለቱ ካልሆነ ደግሞ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
8. በቁ14 ላይ የሚያዘው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መልበስ የፍቅር ዕዳችንን ከመወጣት ጋራ እንዴት ይያያዛል?
9. ለሰዎች ሁሉ የፍቅር ባለዕዳ እንደሆንክ አስበህ ታውቃለህ? የየለት ኑሮህን እንደ ፍቅር ባለዕዳ ብትኖር ህይወትህ በምን መንገድ የሚቀየር ይመስልሃል? ዘወትር ቀንህን ስትጀምር እንደ ፍቅር ባለዕዳ ሆነህ ለመዋል እንድትችል መጸለይን አትርሳ፡፡

# <u>ጥናት ሃያ ዘጠኝ (ሮሜ 14፡1-12)</u>

የጥናት ዓላማ፡ በክርስትያኖች መሃል አከራካሪ የሆኑ ነገሮች እንዳሉ እንድንረዳና በእደነዚህ ዓይነት ነገሮች ላይ ከመፈራረድና ከመናናቅ የልቅ የመቀባበል መንፈስን እንድናዳብር ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹በእምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው፤ አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በአቋሙ ሳትፈርዱበት ተቀበሉት…የሚበላ የማይበላውን አይናቀው፤ የማይበላውም ሚበላውን አይኮንን›› ሮሜ 14፡1-3

1. ሮሜ 14፡1-12 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ ይህ ክፍል የሚያተኩረው በምን ዓይነት ሁኔታዎች ላይ ነው? አከራካሪና አከራካሪ አይደሉም ብለህ በግልህ ከምታምንባቸው ነገሮች ምሳሌዎችን ተናገር፡፡
2. ቁ1 ‹‹በእምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው…›› በዚህ ክፍል በእምነት ደካማ መሆን ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. አንድ ሰው ከቁ1-4 ያለው ክፍል ሊያስተምር የፈለገው ምግብን በተመለከተ ነው ቢል ልክ ነው ትላለህ ወይ? አይደለም ካልክ የዚያ ክፍል ዋና መልዕክት ምን እንደሆነ መጽሀፍ ቅዱስን በመመርኮዝ አስረዳ፡፡
4. በቁ1-4 እርስ በእርሳችን መፈራረድና መናናቅ የሌለበንን ቢያንስ ሶስት ምክንያቶች ማየት እንችላለን፡፡ እነዚህን ሶስት ምክንያቶች ዘርዝር፡፡
5. ቁ5 ‹‹እያንዳንዱ የራሱን ውሳኔ ልብ ብሎ ይወስን፡፡›› ሲል በሁሉ ነገር ላይ እያንዳንዳችን የራሳችን የሆነ እውነት ይዘን መሄድ እንችላለን ማለቱ ነው ወይ? ይህ ካልሆነ ምን ለማለት እንደፈለገ አስረዳ፡፡
6. በቁ 10-12 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ ሊያስተላልፍ የፈለገው ሃሳብ ምን ይመስልሃል?
7. ከሌሎች ወገኖች ጋራ ልትስማማ ያልቻልክበት መንፈሳዊ ውይይት ገጥሞህ ያውቃል? ከሆነስ አለመግባባታችሁን በምን መንገድ ፈታችሁት? ከወገኖችህ ጋራ ለሚገጥምህ በመንፈሳዊ ሃሳቦች ላይ አለመግባባት ሲገጥምህ ዛሬ የተማርከው ትምህርት በምን መንገድ ይረዳሃል?

# ጥናት ሰላሳ (ሮሜ 14፡13-23)

የጥናት ዓላማ፡ እውነተኛ ክርስትያናዊ ነፃነት ማለት ያገኘነውን መብት የመጠቀም ጉዳይ ሳይሆን ለሌሎች መታነጽና ለሰላም ስንል መብታችንን አውቀን የማስተላለፍ ጉዳይ እንደሆነ ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ለወንድምህ መሰናክል ምክንያት የሚሆነውን ሥጋ አለመብላት፤ ወይንን አለመጠጣት፤ ወይም አንዳች ነገርን አለማድረግ መልካም ነው።›› ሮሜ 14፡21

1. ሮሜ 14፡13-23 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። ምንባቡ ሲጀምር ‹‹ስለዚህ›› በማለት ነው። ይህ ስለዚህ የሚለው አነጋገር ከየትኛው ሃሳብ ጋራ የተገናኘ ይመስልሃል?
2. እርስ በእርስ ከመፈራረድ ይልቅ ቁ13 ክርስትያን ማድረግ ስለሚኖርበት ነገር ምን ያስተምረናል? ይህ ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ።
3. በቁጥር 13 ላይ ‹‹ቁርጥ ሃሳብ/ውሳኔ አድርግ›› ይህንን ሲል የምትረዳው ነገር ምንድነው?
4. አንድ አይነት ነገር ለአንዱ አማኝ ሃጥያት የሚሆንበት ለሌላው ግን የማይሆንበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል ወይ? ከዚህ አንጻር ቁ14 የሚያስተምረን ትምህርት ምንድነው?
5. በቁ14 ላይ እውነትና ፍቅር በአንድነት የሚሰሩ ነገሮች እንጂ የሚቃረኑ ነገሮች እንዳልሆኑ የሚያስተምረን በምን መንገድ ነው? ይህ ክፍል ስለተግባራዊ ፍቅር ምን ያሳየናል?
6. ቁ18 ‹‹በዚህ ሁኔታ ክርስቶስን የሚያገለግል›› ስለየትኛው ሁኔታ ነው የሚናገረው? የዚህ አይነቱ አኗኗር በዚህ ክፍል መሰረት እንደምንድነው የተቆጠረው? ለምን?
7. አማኞች በፍቅር የመመላለሳቸው ውጤቶች ሆነው በቁ19 ላይ የተጠቀሱት ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው? እነዚህ ሁለት ውጤቶች ሊከተሉ የሚችሉበትን መንገድ አስረዳ።
8. በቁ22 ላይ‹‹ስለ እነዚህ ነገሮች ያለህ እምነት›› የሚለው ስለየትኛዎቹ ነገሮች ነው?
9. ዛሬ የተማርከው እውነት በክርስቶስ ያለህን ነጻነት አጠቃቀም በምን መንገድ ይቀይረዋል? በዚህ ሳምንት መብቴ የምትላቸው ለሰላምና ለሌሎች መታነጽ ስትል ካለማድረግ መቆጠብ ስለሚኖርብህ ነገሮች ወስን፤ ውሳኔህን እንዲያጸና ለጌታ በጸሎት ንገረው።

# ጥናት ሰላሳ አንድ(ሮሜ 15፡1-13)

የጥናት ዓላማ፡ በህይወታችን ሊሆኑ የምንወዳቸው መንፈሳዊ ለውጦች ሁሉ ዋነኛ ግብ አድርገን ልናይ የሚገባን ለእግዚአብሄር ክብር እንደሆነ መረዳት እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ይኸውም በአንድ ልብና በአንድ አፍ ሆናችሁ፤ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክና አባት ታከብሩ ዘንድ ነው።›› ሮሜ 15፡6

1. ሮሜ 15፡1-13 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። ደካማና ብርቱ ተብለው ከሚነገሩት ጳውሎስ ራሱን ከየትኛው ክፍል ይመድባል? ራሱን ከብርቱ ሊመድብ ያስቻለው ምክንያት ምንድነው ትላለህ?
2. በቁ1-2 ያለው ክፍል እንድንረዳ የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ ምንድነው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተዘረዘሩ ለባልንጀራ ልናደርግ የምንችላቸው ሶስቱ ነገሮች ተናገር።
3. ቁ3-5 ባለው ክፍል ውስጥ የመጽናናጽ ምንጭ በመሆን የተጠቀሱትን ነገሮች ዘርዝር።
4. ዛሬ ባነበብነው ምንባብ አኳያ ሲጠና ይህ በቁ5 ላይ ‹‹ክርስቶስ ኢየሱስን ስትከተሉ›› የሚለው ሃሳብ በዋነኛነት የሚጠቁመን የትኛውን ባህሪውን ስንከተል ማለቱ ነው?
5. ቁ5-6 ትን ስንመለከት የአንድነት መንፈስ ሊገኝ ስለሚችልበት መንገድ ምን ይነግረናል?
6. በዚህ ክፍል መሰረት የአንድነት መንፈስ የሚባለው የሚያካትታቸው ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ይህ ማለትስ ምን ማለት ነው?
7. ቁ3 እና ቁ7 ክርስቶስ ለአማኞች ምሳሌ ከሆነባቸው ብዙ ነገሮች መሃል ሁለቱን ይጠቅሳሉ። እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር።
8. በቁ6፤ ቁ7 እና ቁ9 ውስጥ በህይወታችን ለምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ምክንያት ሊሆነን የሚገባ አንድ ሃሳብ ተሰንዝሯል። ይህ የተሰነዘረው ሃሳብ ምን እንደሆነ አስረዳ።
9. የምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ምን ያህል ከእግዚአብሄር ጋራ ይያያዙልሃል? ከዚህ አንጻር ዛሬ የተማርከው ክፍል በምን መግገድ ረድቶሃል?

# ጥናት ሰላሳ ሁለት(ሮሜ 15፡14-32)

የጥናት ዓላማ፡ የቅዱሳን ጸሎት የማያስፈልገው ማንም አማኝ ሊኖር እንደማይገባና፤ ስንጸልይ እግዚአብሄር በራሱ መንገድ መልሱን እንዲመልስ ልባችን የተዘጋጀ ሊሆን እንደሚገባው ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ወንድሞች ሆይ፤ ስለእኔ ወደ እግዚአብሄር በመጸለይ የተጋድሎዬ አጋር እንድትሆኑ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ›› ሮሜ 15፡30

1. ሮሜ 15፡14-32 ያለው ክፍል በእርጋታ ይነበብ። ጳውሎስ በቁ14 ላይ ስለሮሜ ክርስትያኖች ስላለው አመለካከት የሚናገራቸውን ነገሮች ዘርዝር።
2. በቁ17-20 ባለው ክፍል ውስጥ አገልግሎትን በተመለከተ ጳውሎስ የሚኖርባቸው መመሪያዎች በቀጥተኛም ሆነ በተዘዋዋሪ የምታያቸውን ሃሳቦች ተናገር።
3. ‹‹አሁን ግን በእነዚህ አካባቢዎች የምሰራው ስለሌለ…›› ቁ23 ይህንን ማለቱ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሁሉ ድነዋል ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ ነው?
4. ሮሜ 15፡23-29ና ያዕ 4፡13-15ትን በማነጻጸር ተመሳሳይነታቸውን ወይም ልዩነታቸውን አስረዳ። ከዚህ ለህይወታችን የምንማረው ነገር ምንድነው?
5. በዚሁ ቁ23-29 ባነበብነው ክፍል መሰረት በመንፈሳዊ ነገር የባረኩንን ሰዎች የምንባርክበት አንዱ መንገድ ምንድነው ይላል?
6. ሮሜ 15፡28 ጳውሎስ ትልቅ የሆነ ዕቅዱን ከመፈጸሙ በፊት ማድረግ ስለሚፈልገው ነገር ይናገራል። ይህ ማድረግ የሚፈልገው ነገር ምንድነው?
7. ጳውሎስ ቅዱሳኑ በፀሎት እንዲጋደሉለት የሚጠይቃቸው ርዕሶች ምን ምንድናቸው?
8. እግዚአብሄርን የምትጠይቀው ነገር ምንድነው? እግዚአብሄር በራሱ መንገድ መልስ እንዲሰጥህ ምን ያህል ልብህ ክፍት ነው?

# ጥናት ሰላሳ ሶስት(ሮሜ 16፡1-16)

የጥናት ዓላማ፡ ክርስትያን የጌታን ሥራ ከሌሎች ጋራ በመጠመድ በቡድን ለመስራት የሚጥር እንጂ ሁለጊዜ የብቸኛነትን አገልግሎት ብቻ መፈለጉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹ቄርቂስ ወደ ገላትያ፤ ቲቶ ወደ ድልማጥያ ሄደዋል፤ ከእኔ ጋራ ያለው ሉቃስ ብቻ ነው፡፡ ማርቆስ በአግልግሎቴ ስለሚረዳኝ ከአንተ ጋራ ይዘኸው ና›› 2ኛ ጢሞ 4፡10-11

1. ሮሜ 16፡1-16 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ከተጻፈው ስለ ፌቤን ማንነት ምን እናውቃለን? ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህች ሴት ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?
2. ‹‹ለቅዱሳን ተገቢ በሆነው አቀባበል…›› ከዚህ አባባል የምትረዳው ሃሳብ ምንድነው?
3. በቁ3-5 ባለው ክፍል ስለ ጵርስቅላና አቂላ የምታያቸውን ነገሮች በሙሉ ዘርዝር፡፡
4. ስለ አንዲራኒቆንና ስለ ዩሊያን ቁ7 ምን ይናገራል? ሌሎቹ ስለነዚህ ሰዎች የተነገሩ ነገሮች ባይኖሩ በክርስቶስ በማመን መቅደማቸው ብቻ ትርጉም ይኖረው ይመስልሃል ወይ? ለምን?
5. ቁ1፤ ቁ3፤ ቁ6፤ ቁ12 ትንና የመሳሰሉትን ክፍሎች ስታነብ የጳውሎስ ሰላምታ ያተኮረው በምን ዓይነት ሰዎች ላይ ነው?
6. ሰዎችን በሥም እየጠሩ ማመስገን ሊያስከትል ስለሚችላቸው አደጋዎች ጥቂቶቹን ተናገር፡፡ ታዲያ ጳውሎስ ይህንን አደጋ ስላልተረዳ ነው ወይስ ለምን ይህንን ለማድረግ መረጠ?
7. 2ኛ ጢሞ 4፡9-12 ትንና በዚህ ክፍል አብረውት በጌታ ሥራ የሚደክሙትን ሰዎች ሁሉ መዘርዘሩን ስንመለከት ስለጳውሎስ አገልግሎት ምን እንማራለን?
8. የቡድን አገልግሎትን አስመልክቶ የጳውሎስ አገልግሎት ከኢየሱሰ አገልግሎት ጋራ የሚመሳሰልበትን ምን መንገድ ትመለከታለህ?
9. እስከ ዛሬ የነበረህ በቡድን የማገልገል አመለካከት ምን ያህል ከዛሬው ትምህርት ጋራ ይመሳሰላል? ከዚህ ጥናት በተማርከው በህይወት ሊቀየር የምትወደው ነገር ካለ ከወገኖች ጋራ ተካፈል፡፡

# ጥናት ሰላሳ አራት(ሮሜ 16፡17-27)

የጥናት ዓላማ፡ ወንጌልን ከሙሉ ልባችን ያመንና ወንጌሉ የሚነግረንን ለመታዘዝ ፈቃደኞች የሆን አማኞች መለያየትን የሚዘሩ እንዳሉ በመረዳት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡‹‹ወንድሞች ሆይ፤ መለያየትን ከሚፈጥሩትና የተማራችሁትን ትምህርት በመቃወም በጉዟችሁ መሰናክል ከሚያደርጉት እንድትጠነቀቁ አሳስባችኋለሁ፤ ከእነርሱም ራቁ። ሮሜ 16፡17

1. ሮሜ 16፡17-27 ያለውን ክፍል በአንድነት አንብቡት። ቁ17-18 ያተኮረባቸው ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? የተጻፈላቸው ሰዎች ከእነዚህ በቁ1 ከተጠቀሱት ሰዎች ጋራ ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት ምን ይላል?
2. በቁ17-18 ስለነዚህ ጳውሎስ እንዲጠነቀቁ ስለሚናገራቸው ሰዎች ልናውቅ የምንችላቸውን ሃሳቦች በሙሉ በመዘርዘር ተናገር።
3. ሮሜ 15፡3-6 ትና ሮሜ 16፡17-20 ያለውን ክፍል በማንበብ ህብረትን አስመልክቶ የሚገልጡትን ሃሳብ በማነጻጸርና በማወዳደር ተናገር።
4. የሮሜ ክርስትያኖች ቁ19 ላይ ለወንጌል ታዛዥነታቸውን ቢያውቅም ከዚያ በተጨማሪ በእነርሱ ውስጥ ሊያይ የሚፈልገው ባህርይ ምንድነው? ኢየሱስ ይህንን ባህርይ በተመለከተ የተናገረው ትዝ የሚልህ የትኛው ጥቅስ እንደሆነ ተናገር።
5. ሮሜ1፡8፤ 16፡19 እና 16፡25 ትኩረት በመስጠት ይነበብ። እነዚህን ሶስት ጥቅሶች በመጭመቅ አንድ ልናጤነው የምንችለው ሃሳብ ምንድነው?
6. ለምንድነው ስለሚለያዩና ስለሚከፋፍሉ ሰዎች እየተናገረ ባለበት በቁ20 ላይ ሰይጣንን በመሃል ማስገባት ያስፈለገው?
7. በሮሜ 16፡21-24 ጳውሎስ የሚዘረዝራቸው ሰዎች እነማን ናቸው? እነዚህን ሰዎች ሐዋርያው ከሚያስተዋውቅባቸው መንገዶች ዋና ዋናዎቹን ጥቀስ? በሮሜ 16፡1-16 በሩቅ ላሉትና በዚህ ክፍል ደግሞ አብረውት ያሉትን አገልግሎት ሁኔታ መዘርዘሩ ምን ያስተምረናል?
8. ለምንድነው በመሰነባበቻ መሃል መለያየትን የሚፈጥሩ ሰዎችን ጉዳይ ያለቦታው ያስገባው?
9. ቅዱሳንን መለያየት በጌታ ፊት አጸያፊ መሆኑን ምን ያህል ተረድተሃል? ሮሜ 14፡19 የሚያዘውን ተግባራዊ ለማድረግ የዘወትር ጸሎትህና ትጋትህ አድርገህ ውሰድ።

# <u>ጥናት ሰላሳ አምስት(የሮሜ ማጠቃለያ ጥናት)</u>

የጥናት ዓላማ፡ ሮሜ 1-16 ያሉትን ምዕራፎች ስናጠና የተመለከትናቸውን እውነቶች ጠቅለል ባለ መንገድ ለማየትና እያንዳንዳችን ስለመጽሃፉ ያተረፍነውን መረዳት ለመገምገም፡፡

1. ሮሜ 1፡16-17, 3፡23-24, 5፡1-2, 8፡1-2, 12፡1-2 ትን በአንድነት በማንበብ ለዚህ መጽሐፍ ቁልፍ ጥቅስ ይሆናል የምትለው የትኛው እንደሆነ ተናገር፡፡ ለምን?
2. የሮሜ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ባይኖር ይጎድልብን ነበረ ብለህ የምታስባቸውን ነጥቦች በሙሉ በመዘርዘር ተናገር፡፡
3. በአንተ አመለካከት የዚህ መጽሃፍ መሪ ሃሳብ (Theme) ምንድነው ትላለህ?
4. ከሮሜ መጽሃፍ ውስጥ አንድ ምዕራፍ ምረጥ ብትባል የትኛውን ትመርጣለህ? ለምን?
5. ሮሜን ሊያጠና ለምትመኝለት ጓደኛህ ስለ__________መረዳት ከፈለግህ ሮሜን አጥና ለማለት ከላይ የሚታየውን ባዶ ቦታ ምን በማለት እንደምትሞላው ተናገር፡፡
6. በያዕቆብ 1፡23-24 የእግዚአብሄር ቃል እንደ መስታዋት እንደሆነ ይነግረናል፡፡ የሮሜ መጽሐፍ ጥናት ለህይወትህ በመስታወትነት ያገለገለበትን ቢያንስ አንድ ነገር ተናገር፡፡
7. በዚህ በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሄር አደረገልን ተብለው የተነገሩ ብዙ ትላልቅ ድርግቶች እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ከእነዚህ ከተነገሩን መሃል በአንተ ልብ ውስጥ ትልቁን ሥፍራ የሚይዘው የትኛው ድርጊት ነው?